# የመንግስት እቅድ፤ የወጣቶችም ተስፋ ተምኔታዊ አይደለም!

**ውብሸት 12-26-16**

በአገራችንም ሆነ በሌሎች አገሮች የተለያዩ መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችና ሲቪክ ማሕበራት ወጣትነት ለሚለው ፅንሰ ሃሳብ የተለያየ የዕድሜ ክልል ይጠቀማሉ። ይህ ደግሞ የሚያሳየው ሁሉም አካላትፍረጃውን የሚሰጡት በተመሳሳይ የመመዘኛ መስፈርት ሳይሆን ከቆሙለት ዓላማና ከሚያከናውኑት ተግባር አኳያ በሚከተሉት መርህ ላይ ተመስርተው መሆኑን ነው። ለምሳሌ፤- የተባበሩት መንግስታት ድርጅት ወጣት የሚለውን የማህበረሰብ ክፍል ከ15-24 ዓመት የእድሜ ክልል ውስጥ የሚገኝ ነው ሲል፤ የዓለም ጤና ድርጅት ደግሞ እድሜው ከ10-24 ዓመት የሆነ ሁሉ ወጣት ነው ይላል። በሌላ በኩል፤ የኢትዮጵያ የማሕበራዊ ደህንነትና ልማት ፖሊሲ ከ15-24 ዓመት የዕድሜ ክልል ውስጥ የሚገኘን ማንኛውንም ሰው ወጣት በማለት ይተረጉማሉ። ይህ ልዩነት በአገራት ደረጃም ይታያል፤ ከእነዚህ ውስጥ በአፍሪካ አህጉር ያለውን ለማሳያነት ብንወስድ እንኳን፤ ዑጋንዳ ከ12-30 ዓመት፤ ደቡብ አፍሪካ ከ14-28 ዓመት፤ ናይጄሪያ ከ18-35 ዓመት፤ ጅቡቲ ከ16-30 ዓመት ያሉትን የህብረተሰብ ክፍሎች ወጣት በማለት ይፈርጇሉ።

አገራቱም ሆኑ ድርጅቶቹ ወጣትነትን በእድሜ ጣሪያ ለመወሰን ይለያዩ እንጂ በሌሎች ማህበራዊ እሳቤዎች ግን በአብዛኛው ይስማማሉ። በዚህም ወጣትነተ ተስፋ ያዘለ፤ ነገን ለመረከብ የታጨ፤ አፍላነትና አዲስ ነገር ናፋቂነት የተሞላ ስለመሆኑ ሁሉም ይቀበላሉ። በእኛም አገር የማህበራዊ ደህንነትና ልማት ፖሊሲ ውስጥ ከእድሜ ክልሉ ባሻገር ትልቁ ትኩረት ያረፈው በማህበራዊው እሳቤ ላይ ነው።

ወጣቶች በአገር የልማት ግስጋሴ ውስጥ የማይተካ ሚና አላቸው። የነገ አገር ተረካቢ፤ የትውልድ አስቀጣይ የመሆናቸውን ያህል በዛሬ ቁመናቸው በአካልና በመንፈስ ጠንክረው ሊገኙ ይገባል። የመንፈስ ጥንካሬያቸው ደግሞ የሚመሰረተው በትምህርት ነው። በመደበኛ ትምህርት ያገኙትን እውቀትና ክህሎት በማህበራዊ ተሳትፏቸው ወደላቀ ደረጃ ያሸጋግሩታል። የወጣቶችን ተሳትፎና ተጠቃሚት ለማረጋገጥ የግንባር ቀደምትነቱን ሚና እራሳቸው ወጣቶቹ መወጣት እንደሚገባቸው ቢታመንም፤ ከቤተሰብ ጀምሮ ህብረተሰቡን ያጠቃለለና መንግስትንም የጨመረ የጋራ ኃላፊነት ይጠበቃል። ወጣቶች ራሳቸውን በማብቃትና በማደራጀት ለነገ ህይወታቸውና የአገር ተረካቢነታቸው ሲተጉ ይህን ጥረታቸውን በመደገፍ ረገድ ጉዳዩ የሚመለከታቸው አካላት በሙሉ በተቀናጀ አኳኋን ተንቀሳቅሰው የመደገፍ፤ አቅማቸውን የመገንባትና የማብቃት ኃላፊነት ይጠበቅባቸዋል። በዚህ ረገድ ትልቁ ወጣቶችን የማብቃት ኃላፊነት ደግሞ የሚወድቀው በመንግስት ላይ ነው።

በኢትዮጵያም መንግሥት ለወጣቱ ማህበረሰብ ተገቢውን ድጋፍ ለማድረግ የወጣቶች ተጠቃሚነት ፓኬጅ በ1998 ቀርጾ ሥራ ላይ አውሏል። ፓኬጁ በአገር ደረጃ የወጣቶችና ስፖርት ባህል ሚኒስቴርን፤ በክልሎች ደግሞ የወጣቶችን ቢሮዎች ሁሉን አቀፍ ኃላፊነት ሰጥቶ የሚተገበራ ነው። ባለፉት ዓመታትም ወጣቶችን ለማብቃት፣ የሀብት ባለቤት ለማድረግና፤ ስራ ፈጣሪ ሆነው አገር ተረካቢ ለማድረግ በተቋማት እና በሌሎች አደረጃጀቶች አማካኝነት ስትራቴጅዎች ተቀርፀው ወደ ተግባር ተገብቷል። ይሁን እንጂ፤ መንገዱ ሁሉ ደልዳላ ተግባራቱ ሁሉ አልጋ ባልጋ አልነበሩም። ፓኬጁና ስትራቴጂዎቹ ወደመሬት ሲወርዱ በርካታ ተግዳሮቶች ገጥመዋቸዋል። እነዚህ

ተግዳሮቶች አንዳንዶቹ በራሳቸው በስትራቴጅዎቹ የግልጽነትና እጥረትና አንዳንዶቹ በወቅታዊ ሁኔታዎችአለመመቸት፤ ሌሎቹ በአፈፃፀም ክፍተት የተፈጠሩና የተቀሩት ደግሞ በህብረተሰቡ ዘንድ በነበራቸው አሉታዊ አቀባበል ምክንያት የተከሰቱ ናቸው።

በዚህም ምክንያት በወጣቱ ዙሪያ የሚሰሩ ስራዎች አመርቂ ውጤት ባለማምጣታቸው  ባለፉት ዓመታ የወጣት ስራ አጦች ቁጥር ጨምሮ ታይቷል።

በሌላ በኩል፤ በፌዴራልም ይሁን በክልሎች ደረጃ በጥቃቅንና አነስተኛ ዘርፍ የተሰራው ስራ ያጋጠሙ ተግዳሮቶችን መሻገር የቻለና በወጣቶች ተተግብሮ በወጣቶች ላይ አኮኖሚያዊና ማህበራዊ ውጤት አምጥቷል። በማህበረሰቡ ዘንድም አዲስ የአመለካከት፤ የአኗኗርና የግንኙነት ዘይቤ አስፍኗል። በአገሪቱ ኢኮኖሚ ላይም ቀላል የማይባል ድርሻ አበርክቷል። ሲጀመር በዘርፉ ላይ  የነበረውን የአመለካከት ዝንፈት ወደጎን ትተው ወደተፈጠረላቸው መልካም አጋጣሚ ሳያመነቱ የገቡ በርካታ ወጣቶች እራሳቸውንና ቤተሰባቸውን ለውጠው የሀብት ባለቤት ሆነዋል።

በጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች በህብረት ተደራጅተውና በግል ተሰማርተው ከስራ ፈጣሪነት ወደተጠቃሚነት የተሸጋገሩ፤ እንደስራቸው መስፋትና እንደካፒታላቸው ማደግም የመንግስትን እውቅና አግኝተው ወደመካከለኛ ኢንዱስትሪ ባለቤትነት የተመነደጉ ጥቂት የማይባሉ ናቸው። ይህን በተመለከተ በተለያዩ አካባቢዎች ከሰበሰብኳቸው ማሳያዎች የአንዱ ታሪክ ይህን ይመስላል። ባነጋገርኩበት ጊዜ ስሙን እንዳልጠቅስ ቃል ያስገባኝ ይህ ወጣት ተወልዶ ያደገው አዲስ አበባ ከተማ ውስጥ ነው። የሁለተኛ ደረጃ ትምህርቱን አጠናቅቆ ዩኒቨርሲቲ ገብቶ ተመርቋል። ታሪኩ የሚጀምረውም ከምረቃ በኋላ ነው። እንዲህ ይላል፤ -

እኔ በኢንጅነሪንግ ዘርፍ ከባህርዳር ዩንቨርሲቲ ተመርቄ ስወጣ ልክ እንደወጣሁ ስራ አማርጬ የምቀጠር ይመስለኝ ስለነበር የማስበው ስለቅጥር ብቻ ነበር። ሆኖም ባልጠበቅሁት ሁኔታ አንድ ዓመት ከጓደኞቸ ጋር ስራ በመፈለግ አሳለፍኩኝ። በርግጥ በሰፈሬ ብዙ የተማሩ ስራ አጦች አልነበሩም። ተስፋ እየቆረጥኩና በራስ መተማመኔ እየተሸረሸረ ሲመጣ ሰፈሬ ውስጥ ብሎኬት ለማምረት በአነስተኛና ጥቃቅን ከሚደራጁ ልጆች ጋር ተደራጅሁና ስራ ጀመርኩኝ።

ያኔ ጓደኞቼ ተሳለቁብኝ። ዛሬ እነሱ በመንግስት መስሪያ ቤት ውስጥ ተቀጥረው እየሰሩ ነው። እኔ ግን አሁን ድረስ የራሴን ቢዝነስ ፈጥሬ እየሰራሁ ነው። ጓደኞቼ የሚያልሙት መንግስት የሚሰጣቸውን የደመወዝ ጭማሪ ነው። እኔ ደግሞ ያደገና በበርካታ ሰራተኞች የሚንቀሳቀስ ድርጅት ነው። ይህ ሁሉ ግን በቀላሉ የተገኘ አይደለም። ይልቁንም እንደማንኛውም ከታች እንደሚጀምር ስራ ፈጣሪ ውጣውረደችን አሳልፋአለሁ። ከለፉህ ትልክ ትሆናለህ !

የዚህ ወጣት ምስክርነት እንደርሱ በግልና በጋራ የተሳካላቸውን የመወከሉን ያህል በተለያዩ ማህበራዊ፤ ኢኮኖሚያዊና አስተዳደራዊ ችግሮች የተነሳ መስራት ፈልገው ያልሞከሩ፤ ጀምረው በአጭር ያቋረጡ፤ ጠይቀው የተከለከሉ (በመጠን ባይበዙም) ከፍተኛ ቁጥር ያለቸው ወጣቶች በአዲስ አበባም ይሁን በሌሎች ክልሎች መገኘታቸው ሀቅ ነው። አዎን ባለፉት ስድስትና ሰባት ዓመታት በርካታ የስራ እድሎች ቢፈጠሩም በአገሪቱ የስራአጡ፤ በተለይ ደግሞ የተማረው ስራአጥ ቁጥር በከፍተኛ መጠን አድጓል። ከዚህም የተነሳ በወጣቱ ዘንድ ቅሬታ ተፈጥሯል፤ በአደባባይም ተስተውሏል። ይህ ሁሉ በየደረጃው የተገለጸው የወጣቱ ማህበረሰብ ችግር፤ ችግሩ የወለደው ቅሬታና አልፎ አልፎ ቅሬታው የተገለጸበት ተቃውሞና ሁከት እንዳለና እንደሚከሰት መንግስት አስቀድሞ የተረዳው ጉዳይ ነበር። እናም፤  እንደመንግሥት የወጣቶችን ጥያቄዎች የመመለስ ከፍተኛው የኃላፊነት ድርሻ ይእርሱ እንደሆነ ቢያምንም፤ አብዛኞቹ ችግሮቻቸው የሚፈቱት ግን የኢኮኖሚ ተጠቃሚነታቸውን በማረጋገጥ ነው የሚል አቋም አለው። በዚህም ቀደም ሲል የተጀመሩት እንዳሉ ሆነው፤ የወጣቶችን ጥያቄዎች በዘላቂነት ለመመለስ በግልና በጋራ የስራ እድል ለመፍጠር ያስችላቸዋል ያለውን የ 10 ቢሊዮን ብር ተዘዋዋሪ ፈንድ ዕቅድ በያዝነው

2009 ዓ.ም መጀመሪያ ላይ ይፋ አድርጓል። እቅዱ የአተገባበር መመሪያ ወጥቶለት (ይህ በቅርቡ መጀመሩ ተገልጿል) ተግባራዊ ሲደረግ በርካታ ሥራአጥ ወጣቶችን ተጠቃሚ ያደርጋል ተብሎ ይጠበቃል። በሁሉም አካባቢዎች የሚገኙ ወጣቶችን ለኢኮኖሚያዊ ልማት ተጠቃሚነት የማብቃት ዓላማ ያለውና ለዚህ ዓላማ ብቻ የሚውል የወጣቶች ተዘዋዋሪ ፈንድም በአዲስ መልክ ስራውን ይጀምራል ሲጀምር የወጣቶችን ተሳትፎና ተጠቃሚነት በሚያረጋግጥ አኳኋን ጥቅም ላይ እንደሚውል የሚጠበቅ ነው።

በቅርቡ የወጣው የማዕከላዊ ስታትስቲክስ ኤጀንሲ መረጃ፤ መቶ ሚሊዮን ከሚገመተው የኢትዮጵያ ህዝብ ውስጥ 70 በመቶ ያህሉ ከ30 ዓመት በታች ባለው የእድሜ ክልል ውስጥ እንደሚገኝ ያመለክታል። ለእነዚህ ወጣቶች ታስበው የተቀረጹ መርሃግብሮች የኢፌዴሪ ፕሬዝዳንት በበጀት ዘመኑ የፓርላማ መክፈቻ ዕለት ንግግራቸው ላይ «በመንግሥት በኩል በሚታዩ ድክመቶች በተለይ ደግሞ በአድሏዊ እና ብልሹ አሰራሮች ምክንያት ሲደነቃቀፉ የወጣቱ ትውልድ ቅሬታ እንደሚባባስ ታይቷል» ያሉት መንቂያ ደወል ሆኖ የቢሊዮን ብሩ ፈንድ በህጋዊ ማእቀፍ አቀራረፅ፤ እንዲሁም በመመሪያ እና በአተገባበር ስህተት ምክንያት ቅሬታ እንዳይፈጥርና ገንዘቡን በአግባቡ ተጠቅሞ ወጣቶቹ፤ ብሎም አገሪቱ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ለማስቻል በመጀመሪያ በህጋዊ ማዕቀፉ አቀራረፅ ረገድ ቀጥሎም በአተገባበሩ ላይ ብርቱ ጥንቃቄ ሊደረግ ይገባል።

ከዚያም የኢፌዴሪ ፕሬዝዳንት እንዳሉትና ክቡር ጠቅላይ ሚኒስትር ኃይለ ማርያም በቅርቡ እንዳረጋገጡት፤ መንግስት በተመደበው ተንቀሳቃሽ የወጣቶች ፈንድ አጠቃቀምና የፕሮጀክቶች ትግበራ መሰረተ ሃሳቦች ላይ ከሚመለከታቸው አካላትና ከወጣቶች ጋር በመመካከርና ተፈላጊውን የአቅም ግንባታ ድጋፍ በመስጠት የሚያስፈፅም መሆኑ፤ የወጣቶችን ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚነት ለማረጋገጥም ኘሮግራሞቹ በየጊዜው እየተገመገሙ አስፈላጊው የማስተካከያ እርምጃ ይወሰዳል።

መንግስት ባለው የካበተ የአመራር ልምድ፤ እንዲሁም ስራዎች በባለሙያ (ኤክስፐርት) ተጠንተው እየተሰሩ እያንዳንዱ ስራ ወደመሬት ከመውረዱ በፊት በተግባር እየተፈተሸ፤ ተግባራዊ ከተደረገም በኋላ ድክመትና ጥንካሬው እየተገመገመ ለቀጣይ ስራዎች ግብዓት የሚሆንበት አሰራር በአግባቡ ከተተገበረ እቅዱ የማይሳካበት እንዳችም ምክንያት አይኖርም። ውጤቱም የወጣቶችን ጥያቄ መልሶ፤ የማህበረሰቡን ኑሮ አሻሽሎና የአገሪቱንም ገጽታ ለውጦ በኢንዱስትሪ መር ኢኮኖሚ ወደመካከለኛ የኢኮኖሚ እርከን የሚደረገውን ጉዞ በአስተማማኝ ያግዛል ብሎ ተስፋ መጣል ተምኔታዊ አያሰኝም።